# የአውራምባ ማህበረሰብ አመሰራረትና የሚከተለው ፍልስፍና

# ክፍል ሁለት

**(ከጎንደር መልስ - የጉዞ ማስታወሻ)**፣ ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ በአ.አ.ዩ የህግና ፌዴራሊዝም መምህር

## 1. መግቢያ፡-

የአውራምባ ማህበረሰብ በአማራ ብሔራዊ ክልል ደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን ፎገራ ወረዳ ወጂ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በለውጥ አራማጅነቱና በስራ ወዳድነቱ የሚታወቅ ማህበረሰብ እየሆነ መምጣቱን በቀደመው ጽሁፌ ሰፋ አድርጌ መግለጼ ይታወሳል፡፡ ሆኖም አሁንም ድረስ ይህን ታታሪና ስራ ወዳድ እንዲሁም በፍጹም እኩልነት የሚያምን ማህበረሰብ ምን ያህሎቻችን በአግባቡ እናውቀዋለን? ስንቶቻችንስ ነን ማህበረሰቡን ህይማኖት የለሽ በማድረግ በጭፍን ጥላቻ ተነሳስተን ጭምር ሚናቸውን የምናኮስስ? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ስለማህበረሰቡ የማውቀውን ሀቅ ለመመስከር የጀመርሁትን ጥረት በመቀጠል ይህችን አጭር ጽሁፍ እንካችሁ ብያለሁና እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ሀሳቤን ለአንባቢዎቻችሁ እንድታደርሱልኝ ከወዲሁ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

## 2. አጠቃላይ፡-

ቀደም ሲል ጀምሮ በስራ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የሚከተሉት ፍልስፍናና ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው በእጅጉ እየሳበኝ ስለመጣ በነሱ ላይ ጥናትና ምርምር ለማድረግና ሞያየንም በመጠቀም በማማከር ረገድ ልረዳቸው በማሰብ ከማህበረሰቡ መስራች ከሆኑት አቶ ዙምራ ኑሩ ጋር ይበልጥ እየተግባባን ስንመጣ ባደረግነው የሀሳብ ልውውጥም ይሁን ቀደም ሲል እሣቸውን ተከትለው ከመጡ የማህበረሰቡ አባላት ጋር ባካሄድሁት ቃለመጠይቅ ሁኔታውን ይበልጥ ለመረዳት እንደቻልሁትና በክፍል አንድ ጽሁፌ ላይም ስለማህበረሰቡ በሰፊው እንደተረከሁት አቶ ዙምራ ኑሩ ገና በልጅነታቸው ጀምሮ ይህ ለውጥ ፈንጣቂ የሆነ ፍልስፍና ማለትም በስራ የማመን፣ አባካኝ የሆኑ ሁኔታዎችን የማስቀረት፣ የሴቶችን እኩልነት የመቀበል፣ ህጻናትንና ጧሪ የሌላቸውን አረጋዊያንን የመንከባከብ፣ ስርቆትንና ማጭበርበርን አምርሮ የመጥላት በአጠቃላይም በሰው ልጆች እኩልነት የማመንና የመሳሰሉት የተቀደሱ ሀሳቦች እንደተገለጹላቸውና እነዚህን እምነቶች ለሌሎች ለማካፈል ከትውልድ አካባቢያቸው እስቴ ወረዳ እየተነሡ ጎጃምን፣ ወሎንና ጎንደርን ጨምሮ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ሀሣባቸውን የሚቀበልላቸው ሠው ያፈላልጉ ስለነበር ደቡብ ጎንደር አስተዳደር አካባቢ ፎገራ ወረዳ ውስጥ ስንቆ መድሀኒአለም ቀበሌ ውስጥ ሸህ ሠይዴ የተባሉ ሰውና ተከታዮቻቸውን አግኝተው የለውጥ ሃሳባቸውን ሲያካፍሏቸው የመቀበል አዝማሚያ ያዩባቸዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ይበልጥ እየቀረቧቸው ሲመጡ አርብ ቀን በአካባቢው የሚኖሩት ሙስሊሞች ለፀሎት የሚሠበሰቡበት ዕለት ስለሆነ በርከት ያለ ሠው በአንድ ላይ አግኝተው ለውጥ ያዘለና ተራማጅ ሀሣባቸውን በነጻነት፣ ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ ማካፈል የሚያስችል ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡ በሌላ አነጋገር እነዛ የአካባቢው ሙስሊሞች የሚበዛውን ጊዜያቸውን ጫት በመቃምና ያለት በማድረግ ያሣልፉ ስለነበር የሚመገቡትን የእለት ምግብ እንኳ ለማግኘት ከሌላው ማህበረሰብ ዘንድ በመሄድ ለመለመን ይገደዱ እንደነበር ያረጋግጣሉ፡፡ ይህንን አሳዛኝ ዕውነታ በጊዜ የተገነዘቡት ዙምራ ኑሩ ቅርበታቸውንና የሀሳባቸውን ተቀባይነት በመጠቀም የልመናን ነውርነት በማስገንዘብ በተቃራኒው ሠርቶ በማግኘት ራስን የመቻልን ክቡርነት ለእነዚህ ሰዎች ማስተማር ይጀምራሉ፡፡ ልብ በሉ ይህ የሆነው ከ1964 ዓ.ም በፊት በነበሩት የአቶ ዙምራ የወጣትነት ጊዜያት ነው፡፡

ዙምራ ኑሩ በተወሡት ሠዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኙ ሲመጡ በ1964 ዓ.ም የዕስቴ ወረዳ ነዋሪነታቸውን እርግፍ አድርገው በሙተው ወደ እነሼህ ሰይዴ መንደር ጠቅለው ይመጡና አጠገባቸው እየኖሩ የማስተማርና ሀሳባቸውን የማካፈል ስራቸውን ራሣቸው በተግባር እያሣዩ ጭምር አጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ በነገራችን ላይ አቶ ዙምራ ኑሩም ሆኑ ተከታዮቻቸው ጫት አይቅሙም፣

በያለት ስምም ተኝተው አይውሉም፣ የስራ ጊዜያቸውን የሚሻማ ማህበራዊም ሆነ ባህላዊ ክንውን በፍጹም አይፈፅሙም (ቡናም ሆነ አልኮል ነገር አይጠጡም፣ ድግስ በመደገስ በስንት ልፋትና ድካም የተገኘን ሀብት ለተወሰነ ጊዜ ደስታ ሲባል አያባክኑም)፡፡ ሸህ ሠይዴ በ1973 ዓ.ም ከዚህ አለም ሲለዩም ሲዷቅ የሚባል ሰውና ውድሠው የተባሉት የሸህ ሠይዴ ባለቤት ዙምራ ኑሩ ወደሚኖሩበት መንደር በመሄድ ሙሉ በሙሉ የሀሣባቸው ተጋሪ መሆናቸውን በማረጋገጥ አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ በ1978 ዓ.ም ላይ ደግሞ ማህበረሰቡ የህብረት ስራ ማህበር መስርቶ የማህበረሰቡ አባላት አሁን በሚገኙበትና ቀደም ሲል አርባአምባ ተብላ ትጠራ በነበረችው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በማህበረሰቡ ስም አውራምባ በመባል በምትታወቀው መንደር መኖር ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጅ የደርግ-ኢሠፓ አምባገነን መንግስት አቶ ዙምራን በጥርጣሬ አይን ይመለከታቸው ስለነበር / ከኢህአዴግ ጋር ግንኑነት ፈጥረዋል በሚል ስጋት/ የአዲሱን ሃሣብ ዋነኛ አቀንቃኝ የሆኑትን ዙምራ ኑሩን አስሮ ተራማጅ የሆነውን የለውጥ ሃሣባቸውንም ለሌላው የክልሉ ማህበረሰብ በነጻነት እንዳያሰራጩ በማስፈራራትና በማስጨነቅ ጭምር ለማስቆም ይሞክራል፡፡ በመጨረሻም አስሮ የሚያቆይበት የረባ ምክንያት ሲያጣ የጀመሩትን የለውጥ ሀሳብ እንዲተው አስፈራርቶና አስጠንቅቆ ዙምራን በነጻ ይለቃቸዋል፡፡ ሁኔታው ያላማራቸው ዙምራ ኑሩም በ1980 ዓ.ም ተከታዮቻቸውን ይዘው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ቦንጋ አካባቢ ተሰደው ለአምስት ዓመት ያህል በዛው ከቆዩ በኋላ በ1985/86 ዓ.ም ተመልሰው በቀድሞ መንደራቸው በመኖር የለውጥ ሃሰባቸውንና አዲሱን ፍልስፍናቸውን እንደተለመደው በተግባር አስደግፈው ማስፋፋት ጀመሩ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ከመንግስት ቢሮክራሲው ጀምሮ በአካባቢው ማህበረሰብ በተለይም የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ በሆነው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ የገጠማቸው የማግለልና እንቅስቃሴያቸውን የማንቋሸሽና የማጥላላት ፈተና አይጣል መሆኑን ከበርካታ ተጨባጭ ሁኔታዎች መረዳት ችያለሁ፡፡ ያን ሁሉ ፈተና በዚህ አጭር ጽሁፍ መዘርዘር አስቸጋሪ ስለሆነ እንጅ አንዳንድ ሰዎች በጽሁፍ ሳይቀር ፍልስፍናቸውን ለማጥላላት እንደሞከሩት አይነት ስም ማጥፋትን ጨምሮ ከሌላው ህብረተሰብ እስከማግለል ድረስ የዘለቀ ደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ይህም ሆኖ ጥረታቸውንና የፍልስፍናቸውን ጠቃሚነት በአግባቡ ተመልክቶ ከሶስት አመት በፊት የጅማ ዩኒቨርሲቲ ለአቶ ዙምራ ኑሩ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጣቸው፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎም አንዳንድ ሰዎች የቆየ የጥላቻ ስሜታቸውን ሳይቀር በጽሁፍ መልክ የተለያዩ መጽሄቶችን (ለምሳሌ ቁምነገር መጽሄትን) እና ጋዜጦችን በመጠቀም ጭምር የጅማ ዩኒቨርሲቲ የሰጠውን ዕውቅና ለማጣጣል ሞከሩ፡፡

አውራምባዎች ግን "ውሾቹ ይጮሀሉ ግመሉ ግን ጉዞውን እንደቀጠለ ነው" የሚለውን አባባል ተግባራዊ በማድረግ ምስጋና ለዙምራ ኑሩና ለተከታዮቻቸው ጽናት እንጅ አሁንማ ማንም ቀባጥሪ ተነስቶ የተለመደውን አይነት ጥላሸት ለመቀባትና የንፁህን ሰዎችን ታሪክ ለማጉደፍ እንዲሁም መልካም ስራ የሠሩ ተቋማትንና ግለሰቦችን ታላቅ ክንውን አሣንሶ ለማሣየት ቢሞክር ትርፉ መላላጥ መሆኑን አሁንም በጣም የዘገየ ቢሆንም ቢገነዘብ መልካም ነው የሚል መልክት በዚህ አጋጣሚ ማስተላለፍም እፈልጋለሁ፡፡ ለማንኛውም የጅማ ዩኒቨርሲቲ ለማህበረሰቡ መስራችና መሪ ለዙምራ ኑሩ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሲሰጥ መነሻ አድርጎ የወሰዳቸውን የዙምራ ኑሩንና የማህበረሰቡን አበረታች ፍፃሜዎች በምሳሌ አስደግፎ ለማሳየት ያህል ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች በዝርዝር እንመልከት፡፡

እነዚህ ማሳያዎች ደግሞ በዙምራና በተከታዮቻቸው ብርቱ ጥረት ላለፉት አርባ አመታት የተከናወኑ ሲሆኑ በመካከላቸው ያለው ግንኙነትም በጋራ ድህነትን ለማስወገድ የሚደረግ ምጣኔ-ሀብታዊና ማህበራዊ መስተጋብር እንጅ አንዳንድ አውቆ አበድ ጸሀፊዎች ወይም ግለሰቦች እንደሚሉት መንፈሣዊ ወይም ኃይማኖታዊ ትስስር የፈጠረው ግንኙነት ብቻ አለመሆኑን ሊያረጋግጡ ይችላሉ ብቻ ሣይሆን በየቦታው በርካታ ዙምራዎችና አውራምባዎች እየተፈጠሩ መሆኑንም ጭምር ያሳያሉ ብለን እናምናለን፡፡ በመሆኑም አንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዙምራ ኑሩን ሁለት ጊዜ በመጋበዝ ለመምህራንና ተማሪዎቻቸው ተራማጅ የሆነውን የለውጥ ሃሣባቸውን እንዲያካፍሉ አድርጓል፣ ከዚህም በተጨማሪ አቶ ዙምራና ተከታዮቻቸው በሀዋሣ፣ በመቀሌ፣ በባህርዳርና በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲዎች የበላይ ሀላፊዎች በክብር ተጋብዘው ልምዳቸውንና የለውጥ ሃሣባቸውን (የሚከተሉትን ፍልስፍና) ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አካፍለዋል፡፡

የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት /አመልድ/ 25ኛ ዓመት የምስረታ በአሉን ሲያከብር የማህበረሰቡ ተወካዮች በክብር እንግድነት ተጋብዘው አርአያነታቸውን ለታዳሚው በተግባር እንዲያሳዩ ተደርጓል፣ የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር የባህርዳር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትና የኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስትትዩት አቶ ዙምራንና የተወሰኑ ተከታዮቻቸውን በመጋበዝ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ትምህርት እንዲሰጡና መልካም ልምዳቸውንም እንዲያካፍሉ አድርገዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በሴቶች እኩልነት ላይ ባላቸው የፀና አቋም የተነሣ ማርች 8 በብሔራዊ ደረጃ አዲስ አበባ ላይ በድምቀት ሲከበር በክብር እንግድነት ተጋብዘው እንዲገኙ ከመደረጉም በላይ ልምዳቸውንና ተራማጂ የሆነውን የለውጥ ሀሳባቸውን ለበአሉ ታዳሚዎች እንዲያካፍሉ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባለፈ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፖርኮች ልማት ቢሮ መንደራቸውን (አውራምባን) የቱሪስት ማረፊያ ማዕከል አድርጐ የመረጠው ማህበረሰብ ለመሆን በቅቷል፡፡ ለትምህርት ያላቸውን ጠንካራ ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የክልሉ መንግስት በመደበው በጀት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያስገነባላቸው ሲሆን በራሳቸው ጥረት ያስገነቡትን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እውቅና ከመስጠት ጀምሮ የውስጥ ቁሳቁስ ማሟላቱና አስተማሪ መመደቡ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ መልካም ተግባሮቻቸው ናቸው ብለን እናምናለን፡፡ በዚህም ምክንያት አውራምባዎች ብቻ ሳይሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችም ጭምር ልጆቻቸውን በአቅረራቢያቸው በመልካም ዲስፕሊን ታንጸው እንዲማሩ የማድረግ ዕድል እንዲኖራቸው አድርገዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አጠቃላይ ማሣያዎችን ስንመለከትና ቀደም ሲልም፡-

- "The Role of Media on Community Development: Specially in the Awuramba Community" በአቶ መቅጫ እንግዳየሁ 1997 ዓ.ም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ብዙሀን መገኛ ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት፣

- "Social Transformation among Awuramba Community: the Role of Gender" በአቶ ሠለሞን አጥናፉ፣ 1997 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣

- "The Working Traditions of Awuramba Community and its Contributions to Rural Development" በአቶ ሠይድ መሀመድ 1999 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣
- "The Wisdom of Mediating Family Disputes in the Awuramban Community" በአቶ መርሀጽድቅ መኮነን 2001 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ትሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና
- "Treatments of the Rights of Minorities in Amhara National Regional state: Law and Practice" በአቶ ሲሣይ መንግስቴ 2002 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣

የመሳሰሉት የጥናትና ምርምር ጽሁፎች በአንዱ ወይም በሌላኛው ምክንያት በማህረሰቡ የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ላይ አተኩረው መፃፋቸውን ስንመለከት የአቶ ዙምራ ኑሩ ስርነቀል የለውጥ ሃሣብና እየተከተሉት የሚገኙት ተራማጅ ፍልስፍና የተወሰኑ ተከታዮቻቸውን ሀሳብ ብቻ ሳይሆን የምሁራንንም ቀልብ ጭምር በእጅጉ እየሣበ የሚገኝ ማህበራዊ ፍልስፍና እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

### 3. የሌሎች አውራምባዎች የመፈጠር ሁኔታ፡-

ሌላውና አንዳንድ ሰዎች አሁንም ድረስ መገንዘብ የተሣናቸው ዕውነታ በአሁኑ ወቅት በየአካባቢው በርካታ አውራምባዎች እየተፈጠሩና በሒደትም ፍልስፈናቸው በየትኛውም አካባቢ እየተስፋፋ መመጣቱን ነው፡፡ ለምሣሌ ያህል በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ብቻ ምስራቅ ጐጃም አስተዳደር ዞን ብቸና ወረዳ ወይራ ቀበሌ ላይ ዳግማዊ አውራምባ መመስረቱን፣ በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ውስጥ አዲስ ቅዳም በተባለው አካባቢ ተመሣሣይ ታሪክ መሰራቱን፣ በሰሜን ጐንደር አስተዳደር ዞን አርማጭሆ አካባቢ የትምህርት ቤታቸውን ስያሜ ሳይቀር አውራምባ ብለው የሰየሙ ህዝቦች መኖራቸውን፣ በሰሜን ወሎ መርሣ አካባቢ አስተሣሠቡ እየተስፋፋ መምጣቱን፣ ዋግ ኽምራና ደቡብ ጎንደር- ፋርጣ ወረዳ ውስጥ ተመሣሣይ ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑን እነዚህ ሰዎች ቢያውቁ ኑሮ የዚህ

ዓይነቱ አደናጋሪ ሁኔታ አይፈጠርባቸውም ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡ በአሁኑ ወቅት ማህበረሰቡ ምን ያህል ተፅዕኖ ፈጣሪ እየሆነ እንደመጣ የምገነዘበው ደግሞ ከያኒዎች ሳይቀሩ የግጥም ስንኝ የደረደሩለትና በድምጻቸውም ጭምር እየታገዙ የዘመሩለት/ያቀነቀኑለት/ ማህበረሰብ ከመሆኑም በላይ አውራምባ ታይምስ የሚል ስያሜ የያዘ ጋዜጣ ታትሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ ተነባቢ ሆኖ እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ዙምራ የሚል ፊልም ተዘጋጅቶ የነበረ ከመሆኑም በላይ በየከተሞቹ አውራምባ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው የንግድ ስራዎች መገኘታቸው ሌላው ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት የማህበረሰቡ ማህበራዊ ፍልስፍናና ተራማጅ አስተሳሰብ ከአማራ ክልል ብሎም ከሀገራችን አልፎ በሌላው የአለም ማህበረሰብ ዘንድ በእጅጉ እየታወቀ፣ እየተደነቀና እየተጎበኘ ባለበት በአሁኑ ወቅት ይህን ጠቃሚ የሆነ ፍልስፍና ይበልጥ እንዲስፋፋ ከማድረግና እንደዚህ ያለውን የተቀደሰ የለውጥ ፍልስፍና ተቀብሎ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ የተለመደ አደንቋሪ ጩኸት በተለያዩ አጋጣሚዎች መስማታችንና ሰበብ ፈልጐ አኩሪ ተግባር የፈጸሙትንና እየፈጸሙ የሚገኙትን ጀግኖች የሚያንኳሰስ ዜጋ ማየታችን እኛ ኢትዮጵያውያን ለእድገታችን የሚበጅ የለውጥ ሀሳብ ከውስጣችን ሲመነጭ ለመቀበል ምን ያህል ዝግጁ አለመሆናችንን ብቻ ሣይሆን በአንድ አካባቢና የህብረተሰብ ክፍል የሚመጣን ተግባራዊ ለውጥና ተራማጅ አስተሳሰብ በአይናችን እያየን ጭምር በሙሉ ልብ ተቀብለን ለውጡን ከማበረታታትና የለውጡ ተጋሪና ተቋዳሽ ከመሆን ይልቅ ለማደናቀፍ ምን ያህል ተግተን እንደምንቀሣቀስ ነው፡፡ ለነገሩ ይህ ኋላ ቀርና ጎጂ አስተሳሰብና ድርጊት ቀደም ሲል ጀምሮ ተጣብቶን ስለኖረ ጥላሁን ግዛውንና ዋለልኝ መኮንንን ጨምሮ ፋና ወጊ የለውጥ አራማጅ ወጣት ምሁራንን በራሳችን መሪዎች በአጭር እንዲቀጩ የተደርጎ መሆኑ መች በቀላሉ ይረሳልና፡፡

## 4. *የጋብቻ ሥርዓት በአውራምባ ማህበረሰብ ዘንድ፡-*

ጋብቻ በአውራምባዎች ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ማህበራዊ ስርአት ነው፡፡ የመረዳዳት፣ የመተማመንና የመከባበርም መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ የአንድ ለአንድ ጋብቻን ያበረታታል በተግባርም ይተረጐመዋል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ አንድ ወንድ ከአንድ ሴት በላይ እንዲያገባ አይፈቀድለትም፡፡ ጋብቻውም የሚፈጸመው በሁለቱ ጾታዎች ሙሉ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን የወላጆች ቀጥተኛ ተጽእኖ (ጣልቃ ገብነት) በአውራምባ ማህበረሰብ ዘንድ በምንም መልኩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ጋብቻ የሚፈጸመው ሴቷ 19 ዓመት ወንዱ ደግሞ 20 ዓመትና ከዛ በላይ ሲሆናቸዉና ለመጋባት መወሰናቸውን በፈቃዳቸው ሲያረጋግጡ ሆኖ የጋብቻ ውላቸውን ለማጽናትም ቀለል ባለ ስነስርአት ሁለቱ ተጋቢዎች በአቅራቢያው በሚገኙ ሽማግሌዎች (ሽማግሌዎቹ ወንዶች አሊያም ሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ) አማካኝነት ይፈራረማሉ፡፡ ይህም ማለት ከጋብቻ በፊት ወንዱም ሆነ ሴቷ ሌላ አያውቁም ወይም ከሌላ ሰው ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ከመፈጸም ተቆጥበውና ክብራቸውን ጠብቀው ለጤንነታቸውም ዋጋ ሰጥተው በጋብቻ ይተሣሰራሉ እንጅ፡፡

እንደ አውራምባዎች እምነት የሠርግ ስነስርአት ለማካሄድ በሰፊው መደገስ የሀብትና የጊዜ ብክነትን ያስከትላል፤ በዓመታት ልፋት የተገኘውን ጥሪትም በአንድ ሳምንት ግርግር ያሣጣል፣ ለአንድና ለሁለት ቀን ደስታ ተብሎም ዘላቂ ሕይወትን ሊጐዳ የሚችል እዳ ውስጥ በማስገባት የትዳርን ህይወት ሊያናጋ፣ ድህነትንም ሊያስከትል ካልሆነ በስተቀር ረብ የለውም፡፡ ይልቁንም ለሠርግ ድግስ ይወጣ የነበረውን ሀብትና ንብረት ለተጋቢዎች ጐጆ መውጫና ዘላቂ ህይወት መሻሻል ማዋል ብልህነት ከመሆኑም በላይ ለአካባቢው ብሎም ለሀገር እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል ጠንካራ እምነት አላቸው አውራምባዎች፡፡ ከዛም አልፈው ውድ የሆነውን የስራ ጊዜ ያባክናል እንጅ ለተጋቢዎችም ሆነ ለወላጆቻቸው በአጠቃላይም ለማህበረሰቡ የሚፈይደው አንዳችም ቁም ነገር የለውም የሚል የጸና እምነት ይዘዋል፡፡ በዚህም ሳቢያ የሰርግ ዝግጅት ብሎ ነገር አውራምባዎችን አያሳስባቸውም፣ ምክንያቱም አውራምባዎች የጋብቻን መሰረታዊ ጥቅምና ዘላቂ ህይወት ለማሳመር እንጂ የሚተጉት ለጊዜያዊ ግርግርና ለማስመሰል ድርጊት ስላልሆነ ነው፡፡

## 5. *የሀዘን ሥርዓት በአውራምባዎች መንደር፡-*

አውራምባዎች የሰው ልጅ በቁም እያለ መተዛዘን፣ መረዳዳትና መፋቀር አለበት እንጅ ከሞተ በኋላ ትልቅ ሀዘን ውስጥ መግባት፣ አካልን መጉዳት፣ በዚሁ የሀዘን ስርአት ሰበብም ሥራ መፍታትና

አላስፈላጊ ወጭ ማውጣት በአንድ በኩል የሞተውን ሰው አይመልስም በሌላ በኩል በሕይወት ያለውን ቋሚ ቤተሰብና ምህበረሰብ በእጅጉ ይጐዳልና መቅረት አለበት ብለው በጽናት ያምናሉ ብቻ ሳይሆን ይህንን እምነታቸውንም ያለማመንታት በተግባር ላይ አውለውት እናገኛለን፡፡ በአውራምባ ማህበረሰብ ዘንድ የቅርብ ዘመዳቸውና የቤተሰቡ አባል የሆነ ሰው ቀርቶ የሚወዱትና አብሮአቸው ለአመታት በፍቅር የኖረ ሰው ሲሞት በልባዊ ሀዘን ምክንያት እንባ ማፍሰስና ማዘን ባይቀርም የሞተውን ሰው የተወሰኑ ሰዎች በክብር ወስደው ሲቀብሩ ሌሎቹ የማህበረሰቡ አባላት ወደ መደበኛ ሥራቸው ይሰማራሉ፡፡ በመሆኑም በአውራማባዎች ዘንድ የመረረ ሀዘንም ይሁን ከዚሁ ጋር የተያያዘ የተንዛዛ የሀዘን ስርዓት ማለትም የሰለስቱ፣የሰባቱ፣ የአርባው ወዘተ እያሉ ጊዜና ሀብት አቃጣይ መስተጋብር እንዲቀጥል አይፈቀድም፡፡ እንዳውም “ፈጣሪ በገዛ ፈቃዱ ወደዚች ምድር ያመጣውን ዕቃ ወሰደ” ብለው ስለሚያምኑ ከዛ በላይ ለሞተ ሰው ብዙ ጊዜና ሀብት ማጥፋት ተገቢ ነው የሚል እምነት የላቸውም፡፡

## 6. የአረጋዊያንና ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ በአውራምባዎች ሰፈር፡-

በአውራምባ ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ሰው በእርጅናም ሆነ በጤና እክል ሣቢያ መሥራት ከተሣነው የአረጋውያን ተንከባካቢ ኮሚቴ በኃላፊነት ተረክቦ ማህበረሰቡ በሚመድበው አመታዊ በጀት መንከባከብ ይጀምራል፡፡ ቀሪ ጊዜያቸውንም በተቻለ መጠን ተደስተውና ጤንነታቸው ተጠብቆ እንዲያሣልፉ የቻለውን ያህል ይሠራል በዋነኛነት ኮሚቴው በአጠቃላይ ደግሞ ማህበረሰቡ እንጅ እንደ አሮጌ ዕቃ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን ተጠቅሞ የትም አይጥላቸውም ወይም ለተቋጥሮ የሥጋ ዘመዶች ብቻ አይተዋቸውም፡፡ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት እነዚህን አረጋውያን በጋራ የመንከባከብና ውለታቸውንም የመመለስ ግዴታ እንደአለባቸው አጥብቀው ያምናሉ፡፡

የአውራምባዎች ሌላው አስደናቂ ድርጊት ደግሞ በልዩ ልዩ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡና አሣዳጊ የሌላቸውን ሕጻናት አሥራ ስምንት ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ተንከባክቦና አስተምሮ በማሣደግ ለቁም ነገር ወይም ለወግ ለማዕረግ እንዲበቁ ያደርጋሉ እንጅ በእድላችሁ እዘኑ ብለው ሜዳ ላይ ያለ መጣላቸው እውታ ነው፡፡ በዚህም መልኩ ካልተረዳዳንና ካልተደጋገፍን ከሌሎች የዱርም ሆነ የቤት እንስሣት በምን ልንለይ እንችላለን? የሚል ጥያቄ በማንሣትም የሰውን ልጅ ማህበራዊ እንስሣነትና ማሰብ መቻል አስረግጠው ያወሣሉ ብቻ ሳይሆን በተግባርም አሳይተዋል፣ አሁንም በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአውራምባዎችን አርቆ አሳቢነትና ሰብአዊነት ቁልጭ አድርጎ የሚሳይ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

## 7. ማጠቃለያ፡-

በእርግጥም የአውራምባ ማህበረሰብ መተሳሰሪያ ገመዱን ፍቅር የለውጥ መሳሪያውን ደግሞ ሥራ እንዲሁም እምነቱንም በአንድ ህያው አምላክ አድርጐ ይኸውና ከአራት አሥርት ዓመታት በላይ በጽናት ዘልቋል፡፡ በዚህም ፈተናዎችን እያለፈ፣ ፍልስፍናውን እያበለጸገና ተከታዮቹን እያበራከተ በድል ላይ ድል መጎናጸፍ ችሏል፡፡መላ የማህበረሰቡ አባላትም እርስ በርስ ከመዋደድና ከመከባበር አልፈው ድህነትን በሥራና በሥራ ብቻ ለማሸነፍና ኑሯቸውን ለመለወጥ ሌት ተቀን ተግተው መንቀሣቀሣቸውን የሕይወታቸው አካል አድርገውታል፡፡ሥራን ይወዳሉ ወይም ያፈቅራሉ ማለት ብቻ የአውራምባዎችን ጠንካራ የስራ ባህል ለመግለጽ በቂ ቃል አይደለም ያመልኩታልና፡፡ ይህም ሆኖ ሲሠሩ ያያቸው የአገሬው ሰው በመደመምና በመደነቅ ለምን ይህን ያህል ሥራን እንደሚያፈቅሩ ሲጠይቃቸው ምኑን ሠራነው! ገና ምኑስ ተያዘና ብለው ይበልጥ ሊያስገርመዎትና ሊያስደምመዎት የሚችል ምላሽ ከመስጠት ወደኋላ አይሉም አውራምባዎች፡፡

ይህም ሆኖ የክልሉ መንግስት አካላት አሁንም ድረስ ገና በአግባቡ የተረዷቸው አይመስልም፣ በተለይም በየደረጃው የሚገኙት የአገልግሎት ሰጭ መስሪያ ቤት የስራ ሀላፊዎችም ሆኑ ሞያተኞች እነሱ የሚፈልጉትን አግልግሎት በሚፈልጉት ፍጥነትና አይነት ለመስጠት የተዘጋጁ አይደሉም፡፡ ይህን ያልሁበት ምክንያት አሁንም የአውራምባዎችን የስራ እንቅስቃሴ ከመደገፍ ይልቅ የቆየውን አሰራር፣ ህግና ደንብ እየጠቀሱ ስራ ማጓተትን የሚመርጡ ግለሰቦች ግስጋሴያቸውን ሊያደናቅፉ ሲሞክሩ ይታያሉና ነው፡፡ እንዲሁም መንደሯ በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የጎብኝዎች ማረፊያ ተደርጋ የተመረጠች ቢሆንም የኢንተርኔትና የስልክ አገልግሎቱ የሚያወላዳ አይደለም፣ ወደ መንደሩ የሚወስደው መንገድ ክረምትን ጭምር የሚያገለግል አለመሆንና በሌሎች የመሰረተ ልማት አለመሟላት ችግሮች ምክንያትና መንደሯ በፕላን እንድትመራ በማድረግ የውስጥ ለውስጥ መንገዱን በድንጋይ ንጣፍ ለማልበስ የተመቼ ሁኔታ አለመኖሩ፣ ቋሚ ተክሎችን ለማልማት አለመቻላቸውና ጎብኝዎች የሚያድሩበትና እየተዝናኑ የሚቆዩበት ምቹ የመዝናኛ ቦታ አለመዘጋጀት ወዘተ. በአግባቡ ሊታዩ የሚገባቸው ሁኔታዎች ይመስሉኛል፡፡

እንግዲህ እኔ ከአውራምባዎች ጋር ባሣለፍኳቸው ጥቂት ቀናት በተለይም ከማህበረሰቡ መስራችና መሪ ከሆኑት አቶ ዙምራ ኑሩ ጋር ባደረግሁት ጣፋጭ ጭውውትና ባሣለፍኳቸው ፍሬያማ ጊዜያት ይህንን እንደ ንጋት ጽሀይ

ይበልጽ ብርሀን ፈንጣቂ እውነት ልመሰክር በቅቻለሁ፣ እናንተስ ይህን ውብ ባህል፣ ቀናና ተራማጅ አስተሳሰብ ስትመለከቱና ስታነቡ ምን ተሰምቷችሁና ታስቧችሁ ይሆን? ከቻላችሁ በአካል ሄዳችሁ ጐብኟቸውና በሀሣብም ይሁን በቁሣቁስ በመርዳት ጥረታቸውን ደግፏቸው፡፡ ካልሆነም መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ በማለት ጎዳናውን ልቀቁላቸው እንጅ ግስጋሴያቸውን ለመግታት እንቅፋት አትሁኗቸው የመጨረሻው መልዕክቴ ይሆናል፡፡